# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 171 ነሃሴ 19 2003 ገጽ 1


**የሰሜን አፍሪቃና የመካከለኛው ምሥራቅ ህዝባዊ አብዮቶች የዓለምን አስተሳሰብ በእጅጉ ቀይረውታል። የገዛ ራሳቸውን ህዝብ የሚጨፈጭፉ አምባገነኖችን ዓለም በዝምታ አያያቸውም ። መለስ ሆይ ልብ በል!!! የእለት ጉርስህን ሳይቀር የምታገኘው ከእነርሱ ነውና ፊታቸውን ሲያዞሩብህ አንተ እንደማትኖር፤ ለአንተ የኔቶን ጦር ማዝመት እንደማያስፈልግ አስተውል!!!**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ለምና ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን መቸብቸቡን ቀጥሉአል፣ ለህንድ ኩባንያዎች 500 ሺህ ሄክታር ተጨማሪ መሬት ሊሰጥ ዝግጅቱ መጠናቀቁ ታወቀ

ኢትዮጵያን ለማጥፋት ቆርጦ የተነሳው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ቀደም ብሎ በብዙ መቶ ሺህ ሄክታር ሸጦለት የነበረውን የካራቱሪ ኩባንያን ጨምሮ 500 ሺህ ሄክታር ለም መሬት ለበርካታ የህንድ ኩባንያዎች ለማስረከብ ዝግጅቱ መጠናቀቁን ዘጋቢያችን የውስጥ ምንጮቹን ዋቢ በማድረግ ባስተላለፈልን ዘገባ ገለጸ፡፡

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት ይህን የለም መሬት ሽያጭ ተግባራዊ ለማድረግ በርካታ የህንድ ኩባንያዎች ባለንብረቶች አዲስ አበባ መግባታቸውና የጠየቁትንም ያህል ሰፋፊ ለም መሬት ለመስጠት የዘረኛው አገዛዝ ባለስልጣናት ቃል መግባታቸው ታውቁአል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የደረሰን ዘገባ እንደሚያመለክተው ኩባንያዎቹ በተፈጥሮ አካባቢ ላይ ከፍተኛ ጉዳትን የሚያስከትለውን የአበባና ሌሎችም ሰብሎች የማምረት ተግባር የሚያከናዉኑ እንደሆኑ ታውቁአል፡፡

ቀደም ብሎ ካሩቱሪ በመባል የሚታወቀው የህንድ ኩባንያ ለሚያካሂደው ኢንቨስትመንት 300 ሺሕ ሔክታር መሬት መውሰዱ የሚታወቅ ሲሆን፣ በአሁኑ ሰአት በሃገሪቱ ምእራባዊ ክፍል በሚገኘው የጋምቤላ ክልል እንዲሁም በባኮ በመቶ ሺዎች በሚቆጠር ሔክታር መሬት ላይ እጅግ በርካታ የአካባቢዉን ነዋሪዎች በማፈናቀል በቆሎ፣ ስንዴ፣ ሩዝና ሰሊጥ በማምረት ምርቶቹን ወደውጪ አገር በመላክ ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## አንድ ሰሞን ሲጨፈርለት የነበረው የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አደጋ ላይ መውደቁ ተገለጸ፣ ጃፓን የረጅም ጊዜ ብድር እንድትሰጥ ተጠየቀች

የአባይ ግድብ ግንባታ ወሬ ከመናፈሱ ቀደም ብሎ ኢትዮጵያዊያንን ሲያደነቁር የነበረው የአምስት አመቱ የትራንስፎርሜሽን እቅድ በሃገሪቱ የመገናኛ ብዙሃን መሰማቱ ከተቋረጠ በርካታ ወራቶች የተቆጠሩ ሲሆን እቅዱም በዕርዳታ ብቻ በሚገኝ የገንዘብ ድጋፍ ማሳካት ስለማይቻል፣ የጃፓን መንግሥት አነስተኛ ወለድ ያለው በረጅም ጊዜ የሚከፈል ብድር እንዲሰጠው ዘረኛው አገዛዝ መጠየቁን ለአገዛዙ ቅርበት ያለው ሪፖርተር ጋዜጣ ዘገበ፡፡

እንደ ሪፖርተር ዘገባ የወያኔው አገዛዝ በአምስት ዓመቱ ለማሳካት ያቀዳቸውን የመንገድ፣ የባቡር ሐዲድና የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግንባታዎችን ለማስፈጸም ይችል ዘንድ፣ የጃፓን መንግሥት ከዚህ ቀደም ሲሰጠው ከነበረው ዕርዳታ በተጨማሪ አነስተኛ ወለድ ያለው የረጅም ጊዜ ብድር እንዲሰጥ መጠየቁ ታውቁአል፡፡

የዘረኛው አገዛዝን የትራንስፎርሜሽን እቅድ አፈጻጸም አስመልክቶ አስተያየት እንዲሰጡን የጠየቅናቸው በውጪ ሃገር የሚገኙ የኢኮኖሚክስ ምሁር በሰጡን አስተያየት ፣ የወያኔ እቅድ ድሮዉንም ቢሆን የምእራባዊያንን ቀልብ ለመግዛት በሚል ያናፈሰው ወሬ እንጂ ፍጹም ተግባራዊ ሊሆን የማይችል እቅድ እንደነበር ይታወቃል ብለዋል፡፡ ወያኔ መጉረስ የማይችለውን ጭብጦ ወደ አፉ ለማስገባት እንደሚሞክር አይነት ሰው ይመሰላል ያሉን እኒሁ ባለሙያ፣ እኔ የታሰበው እቅድ አለመሳካት ምንም አያስገርመኝም፣ ነገር ግን የእቅዱን አለመሳካት አስመልክቶ የወያኔው አገዛዝ የሚሰጠውን ምክንያት ለመስማት በጉጉት እየተጠባበቅሁ ነው በማለት አስተያየታቸውን አጠቃለዋል፡፡

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ቀደም ብሎ አከናውነዋለሁ በማለት ይፋ አድርጎት የነበረውን የትራንስፎርሜሽን እቅድ የአለም ባንክን ጨምሮ በበርካታ ታዋቂ ምሁራን ሲተች እንደነበረና ተግባራዊነቱ ገና ከጅምሩ ጥርጣሬ አስነስቶ እንደነበር መዘገቡ አይዘነጋም፡፡

## የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ግብርና ሚኒስቴር “ድርቅ እንጂ ረሃብ የለም“ ማለቱ የአገዛዙን ባለስልጣናት በቀቀንነት ያመለክታል ተባለ

የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የግብርና ሚንስቴር ሚንስትር ዴታ ተብዬዉ ምትኩ ካሣ አለቃው መለስ ዜናዊ የተናገረውን በመድገም በኢትዮጵያ አሁንም ሆነ ባለፉት ሃያ ዓመታት ድርቅ እንጂ ረሃብ የለም ሲል መናገሩ የአገዛዙ ባለስልጣናት በራሳቸው የማይመሩና ጌቶቻቸው ያዘዙአቸውን ብቻ የሚያደርጉ በቀቀኖች ናቸው ሲሉ አንድ የግብርና ሙያ ከፍተኛ ኤክስፐርት ለዘጋቢያችን ገለጹ፡፡

ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉና በግብርና ሚንስቴር ውስጥ ለበርካታ አመታት በአግሮኖሚስትነት ያገለገሉት ከፍተኛ ባለሙያ ለዘጋቢያችን እንደገለጹት ከአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ ጋር ቃለምልልስ ያደረገው ይኼዉ የግብርና ሚኒስትር ደኤታ” በኢትዮጵያ ድርቅ እንጂ ረሃብ የለም”፣ በድርቁ ምክንያት የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ቁጥርም የፊታችን ጥቅምትና ኅዳር በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል በማለት መናገሩ ባለስልጣናቱ ምን ያህል ህሊናቸውን ሸጠው ለሆዳቸው ያደሩና ለኢትዮጵያ ህዝብ ቅንጣት ታክል እንኳን ክብር የሌላቸው መሆኑን ያሳያል ማለታቸውን ገልጸዋል፡፡ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የሊቢያው አምባገነን መሪ የሙአመር ጋዳፊ ውድቀት ለኢትዮጵያዊያን ትግል ተስፋ ሰጪ ነው ተባለ

እንደዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ ቁንጮ መለስ ዜናዊ በሊቢያዊያን ላይ እንደመዥገር ተጣብቆ ላለፉት አርባ ሁለት አመታት የሊቢያዊያንን ደም ሲመጠምጥ የነበረው የሙአመር ጋዳፊ አገዛዝ መንኮታኮት መጀመሩንና ከጋዳፊ ሶስት ልጆች ሁለቱ በቁጥጥር ስር መዋላቸውን የሊቢያ ጊዜያዊ የሽግግር መንግስትና የአለማቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ማረጋገጣቸውን በርካታ የዜና አውታሮች ገልጸዋል።

እንደ ዜና አውታሮች ዘገባ የጋዳፊ ታማኝና ደጋፊ ተደርጎ ይቆጠር የነበረው ሰይፍ አል ኢስላም፣ የሊቢያ አብዮት በተነሳ ማግስት ንቀት የተሞላባቸውን ቃለምልልሶች በመገናኛ ብዙሀን ተገኝቶ ይሰጥ የነበር ሲሆን በርካታ የጦር ሰራዊት እንዳለውም ሲዘገብ ቆይቱአል፣ ፣ ይሁን እንጂ፣ አማጽያኑ ባለፈው ዕሁድ የትሪፖሊን ከተማ አብዛኛውን ክፍል ሲቆጣጠሩ እጁን ለተቃዋሚዎች ሰጥቶ እንደነበረ ሆኖም እስከዛሬ ባልታወቀ ሁኔታ ከነበረበት ቁጥጥር ሥር ወጥቶ በአደባባይ የታየ መሆኑንና የሙአመር ጋዳፊ አገዛዝ ያላከተመለት መሆኑን ሲደነፋ በአልጀዚራ ተሌቪዥን ታይቶአል። ሰይፍ አልእስላም በሊቢያ የተነሳውን ህዝባዊ አብዮት ለመደፍጠጥ በወሰደው የሃይል እርምጃ ከአባቱ ሙአመር ጋዳፊ ጋር በአለማቀፉ የወንጀል ፍርድ ቤት ከሚፈለጉት የሊቢያው አምባገነን ተባባሪዎች አንዱና ዋነኛው ነው ተብሎአል።

ቀደም ብሎ በሊቢያ መንግስት የመገናኛ ብዙሃን የጋዳፊ የማስታወቂያ ሚኒስትር የሆነው ሙሳ ኢብራሂም በጋዳፊ እዝ ሥር 65 ሺ ዘመናዊ ስልጠናን የወሰዱ አስተማማኝ ወታደሮች አሉ በማለት ሲደነፋ የቆየ ቢሆንም አለ የተባለው ሠራዊት ህዝባዊ አመጽ የወለዳቸውንና ምንም አይነት ወታደራዊ ሥልጠና ያልወሰዱትን አማጽያን መቋቋም ተስኖት እየተፈረካከሰ መሆኑ ካለፈው ዕሁድ ጀምሮ አብይ የአለም ዜና ሆናአል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት በአገር ውስጥ ካሉ ወጣቶች ጋር በሊቢያ ወጣቶች የተሰራውን ታሪክ አስመልክቶ ባደረገው ቃለምልልስ ወጣቶቹ ሊቢያዊያን ባከናወኑት ታሪክ መማረካቸውንና ኢትዮጵያም ውስጥ ተመሳሳይ ታሪክ ለመስራት ፍላጎት እንዳላቸው መግለጻቸው ተዘግቦአል።

ኢሳት በዘገባው የፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የሆነው ተመስገን ደሳለኝ ባለፈው አርብ ሞት የማይፈሩ ወጣቶች በሚል ርእስ በጻፈው ጽሁፍ የኢትዮጵያ ወጣቶች ለለውጥ እንዲነሱ ጥሪ ማቅረቡን ገልጾ ተመስገን በጽሁፉ " ወጣትነት ሆይ! ብትቀበለውም ባትቀበለውም ሀገር ማለት ወጣትነት ማለት ነው። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የኢትዮጵያ የብር ኖት አቅም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየደከመ ነው፣ የባለ 200 ብር ኖት ለማተም ዝግጅት እየተደረገ መሆኑ ታወቀ

በዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ የጉልበት አገዛዝ ስር የወደቀቺው ኢትዮጵያ የብር የመግዛት አቅም እያሽቆለቆለ መሄዱ በተደጋጋሚ የተገለጸ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በግብይት ላይ ከሚገኙ የብር ኖቶች ከፍተኛ ነው ከሚባለው ከባለመቶ ብር ኖት በተጨማሪ፣ የ200 ብር ኖት ገበያ ውስጥ እንዲገባ ለማድረግ ዝግጅቱ መጠናቀቁን የውስጥ ምንጮቻችንን በመጥቀስ ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ ገለጸ።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት፣ የብር ምንዛሪ አቅም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሽቆለቆለ መውረድ በገበያ ላይ ከፍተኛ የሆነ ግሽበትን ከማስከተሉ በተጨማሪ እስካሁን ድረስ ከፍተኛ የሚባለው የአንድ መቶ ብር ኖት ዋጋ እያጣ በመምጣቱ ዘረኛው አገዛዝ የ200 መቶ ብር ኖት ለማተም ዝግጅቱን እንዳጠናቀቀ ታውቁአል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያዊያንን ኑሮና የኑሮ ደረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያጨለመና የሰቆቃ ኑሮን እንዲገፉም እያደረገ ከመሆኑም በላይ አሁን ያለው የብር ኖት የመግዛት አቅም እጅግ እየወደቀ በመምጣቱ ባለ 200 ብር ኖት ገበያ ውስጥ ማስገባትን እንደምፍትሄ አድርጎ ማቅረቡ ታውቁአል።

የባለ 200 ብር ኖት ገንዘብ ህትመት በሃገሪቱ እየታየ ያለውን የዋጋ ግሽበት አስመልክቶ አስተያየት እንዲሰጡን ያነጋገርናቸው አንድ የኢኮኖሚክስ ምሁር በሰጡን አስተያየት ኢትዮጵያ ውስጥ እየታየ ያለው ገደብ የለሽ የገንዘብ ህትመት ቁጥጥር እስካልተደረገበት ድረስ አሁንም ወደባሰ አዘቅት ከማምራት ውጪ መፍትሄ ሊሆን አይችልም:: ይህን እያደረገ ያለው የወያኔ አገዛዝ ደግሞ እንዲህ አይነቱ የሃገር ውድመት ምንም ስሜት የሚሰጣቸው ባለመሆኑ ምን ማድረግ እንደሚገባን ማሰብና መወሰን ያለብን እኛ እንጂ እሱ ሊሆን አይገባውም ብለዋል::

በቅርቡ የዓለም ባንክና ዓለም ዓቀፉ የገንዘብ ድርጅት የኢትዮጵያ መንግስት ገንዘብ ማተሙን እንዲያቆም ማሳሰባቸው የሚታወስ ሲሆን የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አደጋ ውስጥ እንደሚገኝ በይፋ ማስጠንቀቃቸው ይታወሳል።

## ሊቢያውያን እንኳን ደስ ያላችሁ፤ ለኛም ትምህርት ሆናችሁ!!!!

የሊቢያ ህዝብ ለአርባ ሁለት ዓመታት የተጫነበትን የጋዳፊን አገዛዝ ከጫንቃው ለማውረድ ተቃርቧል። የነፃነት ታጋዮች የአገሪቱን ዋና ከተማ - ትሪፖሊ - አብዛኛውን ክፍል ተቆጣጥረዋል።

ኮሎኔል ጋዳፊ ደጋግሞ "ሊቢያ ቱኒዝያ ወይም ግብጽ አይደለችም" እያለ ሲፎክር ነበር። እውነታው ግን ሊቢያ ከቱኒዚያም ሆነ ግብጽ የባሰች ሆና መገኘቷ ነው። ጋዳፊ ከቤን ዓሊም ወይም ከሙባረክ የከፋ አምባገነን እንደነበረ ሁሉ እሱን ለማስወገድ እየተከፈለ ያለው መስዋዕትነትም እጅግ ከፍ ያለ ሆነ። የጋዳፊ አምባገነንነት መክፋት እሱን ለማስወገድ የሚጠይቀው መስዋዕትን አበዛ እንጂ እሱ ራሱ ሶስተኛው ባለተራ ከመሆን አላዳነውም።

የኢትዮጵያ ህዝብ ከሊቢያ ልምድ የሚቀስማቸው በርካታ ቁምነገሮች ቢኖሩም ለጊዜው ሁለት ነጥቦች ላይ ብቻ እናትኩር።

1. ሰላማዊ ትግል ሰላማዊ ሆኖ ላይዘልቅ ይችላል

   ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሰላማዊ ትግል ተመራጭነት የማያጠያይቅ ጉዳይ ነው። ሆኖም ግን ሰላማዊ ትግል ስለተፈለገ ብቻ የሚገኝ ስልት አይደለም። ሰላማዊ ትግልን በሰላማዊነቱ እንዲዘልቅ አምባገነኑ ኃይል በመጠኑም ቢሆን ቁጥብ የሆነ፤ ይሉኝታ ያለው እንዲሆን ያስፈልጋል። ጋዳፊ የጦር ሠራዊቱ አዛዥነትን በልጆቹና ቅርብ ዘመዶቹ አሲዞ፤ ነፃነት ናፋቂውን ህዝብ በአይጥና ውሻ መስሎ "ጨፍጭፏቸው" ብሎ ሲያዝ ህዝብ ራሱን ለመከላከል መሞከሩ ተገቢና ተቀባይነት ያለው ተግባር ነው። ከሊቢያ የምንማረው አንድ ሃቅ ህዝብን በጅምላ ከመጨፍጨፍ የማይመለስ ሥርዓትን ለመለወጥ የተነሳ ሰላማዊ ትግል ወደ ራስ መከላከል ብሎም ወደማጥቃት ቢሸጋገር ተቀባይነት ያለው ተግባር መሆኑን ነው።

2. በአጭር ጊዜ ውስጥ የሰለጠነ ጦርን መግዳደር የሚችል ህዝባዊ ሠራዊት መገንባት ይቻላል

   ውትድርና ሰፊ ጊዜና ሥልጠና የሚሻ ጉዳይ መሆኑ የማይታበል ሃቅ ቢሆንም ቆርጦ የተነሳ ህዝብ ራሱን በአጭር ጊዜ ማደራጀት የሚችል መሆኑ ከሊቢያ የምንማረው ሁለተኛው ቁም ነገር ነው። ከዛሬ ከስድስት ወራት በፊት መሣሪያ ይዘው የማያውቁ ሃኪሞች፣ ጠበቃዎች፣ መምህራን፣ ተማሪዎች .... ዛሬ የጦር ቡድን መሪዎች ሆነው ለማየት ችለናል። አምባገነኖች የቱን ያህል የሰለጠነና የታጠቀ የጦር ኃይል ቢኖራቸውም እንኳን ህዝብ ለነፃነቱና ለመብቱ አምርሮ ሲነሳ፤ የሰለጠነው ወታደር ባልሰለጠነ ህዝባዊ ኃይል የሚሸነፍበት ሁኔታ መኖሩ በዓይኖቻችን አይተናል።

መማር የሚችል ከሆነ መለስ ዜናዊም ከሊቢያ ሊቀስማቸው የሚገቡ በርካታ ቁም ነገሮች አሉ። መለስ ዜናዊ በተለይም የሚከተሉትን ነጥቦች በአንክሮ እንዲያጤን እንመክራለን።

1. "ኢትዮጵያ ቱኒዝያ፣ ግብጽ ወይም ሊቢያ አይደለችም" ማለት አያዋጣም

   ሙባረክን ጨምሮ ጀምሮ ተመሳሳይ ነገር ያላለ አምባገነን የለም። "እኔ የተለየሁ ነኝ፤ እዚያ የነደደው እኔ ዘንድ አይደርስም" ከማለት በጊዜ መፍትሄ መሻት ብልህነት ነው። መፍትሄው ደግሞ ቀላልና ግልጽ ነው - ሥልጣንን በጊዜ ለህዝብ ማስረከብ! ነው።

2. በሠራዊት መተማመን አያዋጣም

   የቱኒዝያና የግብጽ የጦር ሠራዊቶች ለአደራጇቸው አምባነገነኖች አልሆኑም። በጋዳፊ ልጆቹና እጅግ ቅርብ በሆኑ የቤተሰቡ አባላት የሚመራው የሊቢያ የጦር ሠራዊትም ከመሪዎቹ በስተቀር አብዛኛዎቹ የጦሩ አባላት አብረዋቸው አልቆሙም። በዚህም ምክንያት ነው ነብሰ-ገዳዮችን ከሌሎች አገራት ቀጥረው በህዝባቸው ላይ ማሰማራት ያስፈለጋቸው። ሆኖም ግን ይህ በቅጥረኖች የተሞላው ሠራዊት በስድስት ወራት ውስጥ በተደራጀ የነፃነት አርበኛ ጽኑ ትግል ተፈታ። መለስም ትከሻቸው ባበጠ ጄኔራሎቹ ላይ ስላለው እምነት ደጋግሞ እንዲያስብበት እንመክራለን። በቁርጥ ቀን እነሱም አብረውት ላይቆሙ ይችላሉ፤ ቢቆሙም ተከታዮች ከሌላቸው እጅግም የሚፈይዱት ነገር አይኖርም። አዲስ የተገዙት ሁለት መቶ ታንኮችም የሚፈይዱት ነገር የለም። ታንኮች ከተሜን የማስፈራራት አቅማቸው በ97 አልቋል።

3. ሥልጣን ላለመልቀቅ ማንገራገር መጨረሻን ያበላሻል

   ቤን ዓሊ የልጅ ልጆቹ በልተው የማይጨርሱትን ሃብት ዘርፎ በጊዜ እብስ አለ። ሙባረክ ተመሳሳይ እርምጃ መውሰድ ሲችል በማን አለብኝነት በማንገራገሩ እነሆ በወሳንሳ ፍርድ ቤት እየተመላለሰ ይገኛል። የጋዳፊ መጨረሻ ደግሞ ከሙባረክ እጅግ የከፋ እንደሚሆን መገመት ይቻላል። መለስ ሆይ፤ መዘጋጃያ ጊዜህ አሁን ነው!!! የጋዳፊ መልክተኛ በመጨረሻው ሰዓት ያቀረበውን "የእንድራደር" ጥያቄን ያደመጠው ጆሮ አለመኖሩን ልብ በል።

4. ዓለም ተቀይሯል

   የሰሜን አፍሪቃና የመካከለኛው ምሥራቅ ህዝባዊ አብዮቶች የዓለምን አስተሳሰብ በእጅጉ ቀይረውታል። የገዛ ራሳቸውን ህዝብ የሚጨፈጭፉ አምባገነኖችን ዓለም በዝምታ አያያቸውም። መለስ ሆይ ልብ በል!!! የእለት ጉርስህን ሳይቀር የምታገኘው ከእነርሱ ነውና ፊታቸውን ሲያዞሩብህ አንተ እንደማትኖር፤ ለአንተ የኔቶን ጦር ማዝመት እንደማያስፈልግ አስተውል!!!

ውድ ሊቢያውያን ትግላችሁ ሙሉ በሙሉ ዳር እንዳልደረሰ እናውቃለን። ሆኖም እስካሁን ባየነው ኮርተንባችኋል። ሊቢያን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥራችሁ ፍትህ፣ ነፃነት፣ ዲሞክራሲና እኩልነት የሰፈበት ሥርዓት ትገነባላችሁ ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

እኛ ኢትዮጵያዊን ከናንተ ብዙ እንማራለን።

መለስ ዜናዊም ከሊቢያ ህዝባዊ አብዮት ትምህርት ወስዶ ሥልጣኑን ለህዝብ እንዲያስረክብ እንመክራለን። አለበዚያ ግን አወዳደቁ ከሙባረክም ሆነ ከጋዳፊ የከፋ ሊሆን እንደሚችል ከወዲሁ ለማስጠንቀቅ እንወዳለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ለምና ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ከእነዚህ የህንድ ኩባንያዎች በተጨማሪ ትልቅ የእርሻ መሬት የጠየቀው የዘረኛው አገዛዝ ጋሻ ጃግሬ የሼክ አላሙዲ ኩባንያ የሆነው ሳውዲ ስታር ሲሆን ለዚህ ኩባንያ ብቻ 500 ሺሕ ሔክታር መሬት ለመስጠት ዝግጅቱ ተጠናቁአል፡፡ ስዉዲ ስታር በአሁኑ ጊዜ ጋምቤላ ውስጥ በ10 ሺሕ ሔክታር መሬት ላይ በሩዝ እርሻ መሰማራቱ ይታወቃል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በተለይም በሊቢያ ከስድስት ወራት በፊት ጀምሮ የተቀጣጠለው ህዝባዊ አመጽ ፍጻሜ እያገኘ ከመጣ በሁኋላና፣ ሊቢያዊያንም እንደቻይና ያሉ ከሙአመር ጋዳፊ ጋር ያበሩ ሃገራትን ኩባንያዎች ይወርሳሉ የሚል ወሬ መናፈስ ከጀመረ ቦኋላ በኢትዮጵያ ኢንቨስትሜንት ያላት ቻይናና ሌሎችም ኩባንያዎች ስጋት ውስጥ እየገቡ መሆናቸውን በኩባንያዎቹ ውስጥ ተቀጥረው የሚያገለግሉ የውስጥ ምንጮቻችን ገልጸዋል፡፡ በኢትዮጵያ ተመሳሳይ የሆነ ህዝባዊ አመጽ ከተነሳ አደጋ ላይ እንደሚወድቁ ስጋት የገባቸው የነኝህ ሃገራት ኩባንያዎች በቀጣይ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው እያሰቡበት እንደሆነም ተያይዞ የደረሰን መረጃ አመልክቶአል፡፡

## የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ግብርና ሚኒስቴር "ድርቅ እንጂ ረሃብ የለም" . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ባለሙያው እንደተናገሩት ኢትዮጵያ ውስጥ ወደ አስራ አምስት ሚሊየን የሚጠጋና በ አገዛዙ በይፋ የተገለጸ ህዝብ በርሃብ ምክንያት የምግብ ርዳታ ጥገኛ ሆኖ በሚገኝበት፣ ከዚህም ውስጥ ወደ አምስት ሚሊየን የሚሆኑት በአስቸኩአይ የምግብ ርዳታ ውስጥ ተካተው በሚገኙበት በ አሁኑ ሰአት ኢትዮጵያ ውስጥ ድርቅ እንጂ ረሃብ የለም በማለት በአደባባይ መናገር እጅግ አሳፋሪ ተግባር ነው ብለዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ከፍተኛ ኤክስፐርቱ እንደገለጹት፣ በግላቸው ኢትዮጵያ ውስጥ በርሃብ አለንጋ እየተቀጣ ያለው ህዝብ ቁጥር አገዛዙ በይፋ ከገለጸው እጅጉን የሚበልጥ እንደሆነ፣ በተለይም ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ በመጣው የኑሮ ውድነት ምክንያት በቀን አንዴ እንኳን ለመመገብ አቅም ያጡ በሚሊየኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን አዲስ አበባ ከተማን ጨምሮ በመላው ሃገሪቱ ከተሞች እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡

በመጨረሻም ለኢትዮጵያዊያን ባስተላለፉት መልእክት የወያኔ አገዛዝ እየፈጸመ ካለው ግፍና በደል መላቀቂያ መንገዱ አንድና አንድ ብቻ ነው ይሄውም፣ አገዛዙን

## የሊቢያው አምባገነን መሪ የሙአመር ጋዳፊ ውድቀት ለኢትዮጵያዊያን ትግል . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

አብዮትስ? ለውጥ ማለት መሰለኝ። ነውጥ አላልኩኝም። የዛሬ አዛውንቶች የትላንት ወጣቶች "ተራራን አንቀጥቅጠው ነጻ እንዳወጡ መቼም ቢሆን ከልብህ እንዳታወጣው። ሞት አይፈሬ እንደነበሩም እንዳትረሳ። ሆኖም ግን ለዛሬ ስራቸው ያንን ድል ማካካሻ አታድርግላቸው። አርአያ አታድርጋቸው። ደርግን ስለጣሉልህ ሳይሆን ለምን ያህል ሰው ስራ ፈጠሩ፣ ምን ያክል ፋብሪካ ገነቡ ብለህ መዝናቸው። ተራሮችን ስላንቀጠቀጡ ሳይሆን የሰሩትን መንገድ፣ የአስፋፉትን የቴሌ አገልግሎት እና የመሳሰሉትን የልማት ስራዎች መለኪያህ አድርጋቸው። ሀገርን ምን ያህል ለኑሮ እንድትመች እንዳደረጉልህ ገምግም። ምክንያቱም ይሄ ሲሆን ነውና ነው በስልጣን መቆየታቸው ተገቢ የሚሆነው። ይሄ ከብሄራዊ ውትድርና ታደግንህ፣ ከመታፈስ ገላገልንህ፣ ከቀይ ሽብር አተረፍንህ የሚሉትን እርሳው ፣ እሱ ታሪክ እንጅ ዳቦ በሻሂ አይደለምና።" ማለቱን ገልጹአል። ተመስገን በጽሁፉ ማጠቃለያ ደግሞ " በዚህ በኛ ዘመን የየትኛውም ሀገር ወጣት በረሀብ ሞቶ አያውቅም። ህግ እስካልጣስክ ድረስ ሞትን አትፍራ። ግፍና ጭቆና የወጣቶች ሸክም አይደለም። ጭቆናና ወጣትነት ከተገጣጠሙ ሰኔና ሰኞ እንደማለት ነው። ወጣትነት አብዮት ነው። ቦአዚዝም ልክ እንዳንተ ወጣት ነበር። ያውም ወጣት የነብር ጣት።" ሲል የኢትዮጵያ ወጣቶች ህግን አክበረው ለለውጥ እንዲነሱ መምከሩ ታውቁአል።

## የግንቦት7 አላማ ምንነት፤ ለምንና እንዴት በሚል ርዕስ ከታተመው የግንቦት7 መጽሃፍ የተወሰደ ( ክፍል 2 ካለፈው ሳምንት የቀጠለ )

### እቃ ወይም ባሪያ የመሆን ፍላጎት

ሰብአዊ ማንነታችንና ህሊናችን የተሰራበት ድርና ማገሩ ነጻነት ነው፡፡ ከፍጥረታት ራሳችንን ለይተን ማየት ካስቻለን ግንዛቤ አንስቶ ለትንሹም ለትልቁም ድርጊት ለምናደርገው ውሳኔ መሰረቱ ነጻነት ነው፡፡ ነጻነት ነዝናዛ ነው፡፡ ነጻነታችን በራሳችን በግላችን ውሳኔ ከመወሰንና ወደፊት ከመራመድ ውጭ ምርጫ የሌለን መሆናችን ያለማቋረጥ ያሳስበናል፡፡ ይህ ነጻነት «ብል ሰው በመሆን መኩራት ብቻ አይደለም እንደሰው ኑር» የሚል የማያቋርጥ ፈተና ከፊታችንን ይደነቅራል፡፡ አንዳንዱ ፈተና የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ሃገር በውጭ ወራሪ እጅ ወድቃለች። ይህ ወራሪ እየረገጠ በገዛ ሃገርህ ሁለተኛ ዜጋ አድርጎ ሊገዛህ የመጣ ነው፡፡ ሃብትና ቅርስ የሌለህ፣ የአምስት ህጻናት አባት ነህ፡፡ ለእናትህ አንድ ልጅ ነህ፡፡ ከአባትህ ሞት በኋላ የምትወዳት አቅሟ የደከመ እናትህ የምትጦረው ባንተ ነው፡፡ ይህን ሁሉ የቤተሰብ ሃላፊነት ትተህ፣ ለቤተሰብህ ለሃገርህ ነጻነት ለመታገል፣ በዚህ ትግልም የተነሳ እንደወጣህ ለመቅረት እንደምትችል እያወቅህ ነጻነቴን እመርጣለሁ ትላላህ ወይስ የቤተሰብን ሃላፊነት ምክንያት በማድረግ አንተንም የምትወዳቸውን ልጆቸህንና ቤተሰቦችህን በባርነት ማኖርን ትቀበላለህ፡፡ ነጻነታችን እንዲህ አይነቱን አሰቃቂ ምርጫ ይዞ የሚመጣባቸው ወቅቶች አሉ፡፡

በእንዲህ አይነቱቶቹ ፈታኝ ወቅቶች የሚቀርቡልን አማራጮች ስቃያችንን የሚያበዙ ይሆናሉ፡፡ ጭንቀታችን ሲበዛ ሁኔታውን በድፍረት ተቋቁመን አንዱን በመምረጥ ፈንታ የሰውነት እጣችንን መራገም እንጀምራለን፡፡ እኛ ከመወሰን ይልቅ አንዳች ሌላ ፍጥረት እንዲወስንልን እንመኛለን፡፡ እንዲህ አይነቱ አስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ ብዙ ጊዜ ሰዎች ሲገቡ ምነው «ጆሮዬ ባይሰማ፣ አይኔ ባያይ፣ ባልተፈጠርኩ፣ ምነው ድንጋይ ባደረገኝ» የሚሉ ስሜቶች በውስጣቸው መንሸራሸር ይጀምራል፡፡ እራሳችንም ሆንን ባቅራቢያችን የሚገኙ ሌሎች ሰዎች እንዲህ ስንል በተደጋጋሚ እንደመጣለን፡፡ ይህ ምኞት ሌላ ትርጉም የለውም፡፡ ቀደም ብለን እንደጠቀስናቸው፣ ድንጋይ፣ ዛፍና ላም ሆኜ በተፈጠርኩ የሚል ምኞት ነው፡፡ እነዚህ ፍጥረታት ከነጻ ፍጥረትነት የሚመጣ ጭንቀት እንደሌለባቸው ስለምናውቅ እነሱን ለመሆን መመኘታችን ነው፡፡ ይህ ምኞት ሰው በነጻነቱ የተነሳ የሚደርስበትን ስቃይ ለመቋቋም ሲያዳግተው የሚገባበት ምኞት ነው፡፡ ለብዙዎቻችን ይህ ምኞት፣ በምኞት ደረጃ የሚቀር ጉዳይ ሳይሆን በህይወታችን ደግመን ደጋግመን በስራ የምንተረጉመው ምኞት ሆኖ ይገኛል፡፡ ሌሎች ጥቂት ምሳሌዎችን እንውሰድ፤

በጦር ሜዳ ላይ ህጻናትንና አረጋውያን ነፍሳቸውን ለማዳን የተደበቁበትን ቤተ/አምልኮት «በእሳት አጋይ» የሚል ትእዛዝ ከበላዩ የሚሰጠው ወታደር ትእዛዙን ሳያንገራግር ይፈጽማል፡፡ ከፈጸመ በኋላ ግን ለምን እንዲህ አይነት ግፍ ትፈጽማለህ? ለሚለው ጠያቂው የሚሰጠውን የተለመደ ምላሽ በደንብ ካጤንነው በጣም የሚገርም ነው፡፡ ምላሹ «እኔ ወታደር ነኝ፡፡ ትእዛዝ ሲሰጠኝ መፈጸም አለብኝ። ሌላ ምን ምርጫ አለኝ» ነው የሚለው፡፡ ይህ ወታደር ግን ምርጫ ነበረው፡፡ አለቃውን አልታዘዝም በማለት ከፈጸመው ግፍ መቆጠብ አንዱ ምርጫ ነው፡፡ ሌላው ንጹሃንን መረሸን ነው፡፡ የመጀመሪያው ምርጫ በአለቃው ትእዛዝ መረሸንን ያስከትላል፡፡ ሁለተኛው ምርጫ ንጹሃንን በመፍጀት የገዛ ህይወቱን ማትረፍ ይሆናል፡፡ ሁለተኛው ምርጫም ስናየው ቀላል ይመስላል እንጂ እንደ መጀመሪያው ምርጫ አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም «ህይወቴን ለማትረፍ ስል ህጻናትንና አሮጊቶችን ልፍጅ የሚል ግልጽ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ማንም ሰው አይችልም፡፡ ምክንያቱም የሰው ልጅ ሺህ ጊዜ ነጻ ቢሆን ይህንን ነጻነቱን ተጠቅሞ የሚወስናቸውን ውሳኔዎች የሚገዛ የራሱ የሆነ ማእቀብ ያለው ፍጥረት ነውና፡፡ «ሰው ነጻ ነው። ማናቸውንም ውሳኔ መወሰን ይችላል» ስንል ለውሳኔው መስፈርት ወይም መመዘኛ የለውም ማለት አይደለም፡፡

የእያንዳንዱ ተናጠል ግላዊ ውሳኔ ወደድንም ጠላንም ስለ ሰው ልጆች ተብሎ የሚወሰን ውሳኔ ነው፡፡ ይህ ውሳኔ "በሌላው ላይ የምትወስነው ውሳኔ በራስህም ላይ እንዲወሰንብህ የምትፈቅደው ነውን?" የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡ የጠቀስነው ወታደር «አዎን ሌላ ወታደር ህይወቱን ለማቆየት ሲል እናቴን ልጆቼን ወዘተ ሊገድል ይችላል የሚል ፈቃድ ለሌላው ወታደር እንዲሰጠው ይጠይቃል፡፡ ይህ ደግሞ አስቸጋሪ ነው፡፡ ማለፍ የማይቻል ፈተና ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ከላይ የጠቀስነው ወታደር እፊቱ ከቀረቡለት ሁለት አማራጮች መሃከል አንዱን መምረጥ ሲጨንቀው፣ እስከናካቴው የመወሰን መብት የሌለው ፍጥረት ሆኖ መቅረብን ህሊናው ይመርጣል፡፡

ሰውነቱ የሚገለጸው ልክ ለመጻፊያነት ታስቦ እንደተሰራ ብእር ይመስል፣ እራሱን ለወታደርነትና ለትእዛዝ ተቀባይነት ብቻ የተሳራ አድርጎ በማቅረብ «ወታደር ነኝ ሌላ ምን ማደርግ እችላለሁ» ይላል፡፡ ቀደም ብለን እንዳየነው ይህ ሰው አፈጣጠሩ ከብእሩ የተለየ ነው፡፡ እንዳውም በየጊዜው በሚወስዳቸው ውሳኔዎች እራሱን እየፈጠረ የመሄድ ነጻነት ያለው ሃያል ፍጥረት ነው፡፡ በሰጠነው ምሳሌ ግን እራሱን ከብእሩ የተለየ አድርጎ አያቀርብም፡፡ ብእር ሰሪው በሰራው ብእር እንደሚጽፍበት ሁሉ ይህም ወታደር እራሱን ልክ እንደጠመንጃ እንደቦንብ አለቆቹ ሊገለገሉባቸው እንሚችሉባቸው ሌሎች መሳሪያዎች ራሱን ግኡዝ ነገር አድርጎ ያቀርባል፡፡ ይህንን ነው በርካታ ፈላስፎች «በእያንዳንዱ የሰው ፍጥረት ውስጥ ነጻነት የሚፈጥረውን ሸብር ለመሸሽ ሲባል እቃ የመሆን ፍላጎትና አደጋ አለ» የሚያስብላቸው፡፡

እኛ ከምንወስን ሌሎች እንዲወስኑልን፣ የሚወስንልን ከጠፋም እኛ ራሳችን ውሳኔ በሚፈልጉ ጉዳዮች ላይ መወሰን የማንችል ፍጥረቶች አድርግን የምንቀመጥበትን ህሊናዊ ሁኔታ እናመቻቻለን፡፡ ህሊና ካለው ፍጥረትነት ወደ ግኡዝ ፍጥረትነት፤ ወደማይለማና የማይሳማ ፍጥረትነት ወደ እቃነት ወደ ባርያነት የመቀየር ሌላ ግፊት፣ ሌላው ከሰው ልጆች የማይለየው ባህርይ ነው፡፡

እውነታው ግን አንድ ግለሰብ ከማናቸውም እራሱ ለራሱ በህይወቱ ከሰጣቸው ማህበራዊና ግለሰባዊ ሚናዎቹ አስቀድሞ ሰው ነው፡፡  ወታደር ነኝ፣ አባት ነኝ የድርጅት አባል ነኝ ወዘተ የሚባሉ ሚናዎች ከሰውነታችን በኋላ የመጡ እኛው ለእኛው የሰጠናቸው ናቸው፡፡ ስንፈጠር የግንቦት 7 አባላት እንድንሆን ምርጫ ሳይኖረን የተፈጠርን አይደለንም፡፡ የግንቦት 7 ድርጅትን ተሰባስበን የፈጠርነው፣ አበላቱ የሆንነው እኛው ነን፡፡ ይህ ድርጅት በሰውነታችን ልንቀበለው የማይገባውን ውሳኔ ወስኖ ስናገኘው ምን ማድረግ ይቻላል? የድርጅት ውሳኔ ነው፤ እኔም የድርጅት አባል ነኝ የሚሉ አቋሞች ይዘን ከተገኘን፣ ከላይ ስለወታደሩ ባነሳነው  ምሳሌ ወታደሩ ከወሰደው አቋም የተለየ አይሆንም፡፡ ይህ አካሄድ ነጻነት ካለው ፍጥረትነት ራስን ወደ እቃነት የመቀየር አቋም ነው፡፡

ከላይ የጠቀስነው በሰው ተፈጥሮ ውስጥ ያለውን እቃ/ግኡዝ የመሆን ዝንባሌ የሚያበረታቱ ሌሎች ተጨማሪ ግፊቶች አሉ፡፡ «ራሳችንን እቃ የማድረግ ዝንባሌ ይዘን እንደምንፈጠርና ህይወትም ከእዚህ ዝንባሌ ጋር የሚደረግ የማያቋርጥ ትግል ነው» ያልነው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሌላው የሰው ልጆች ተፈጥሮ ሌላውን ሰውን እንደ እቃ የማየት ዝንባሌን የሚካትት መሆኑን መረዳት ይገባናል፡፡ ይህ እውነታ የሚመነጨው ስለፈለግነው ሳይሆን ሁኔታዎች በእዚህ መንገድ ተዘጋጅተው የተቀመጡ በመሆናቸው የመጣ ነው፡፡ ይህን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለመረዳት እያንዳንዳችን ከፊታችን ወይም ከጎናችን ያለውን ሌላ ሰው እንመልከት፡፡

ይህ ሰው በካበቢያችን እንዳለ መረዳት የምንችለው በዙሪያችን እንዳሉ እቃዎች እንደ ጠረጴዛው እንደ ወንበሩ ሲከሰት ብቻ ነው፡፡ በቀለሙ፣ በቅርጹ፣ ከእኛ በተወሰነ ርቀት በመገኘቱ በሚኖረን ግንዛቤ ነው አንድን ሰው በአጠገባችን በአካል ለመኖሩ የመጀመሪያውን ግንዛቤ መያዝ የምንችለው፡፡ ይህ ማለት እያንዳንዱ ሰው በአቅራቢው ያለውን ሌላ ሰው በቅድሚያ የሚያውቀው በራሱ ውስጥ በሚያገኛቸው ስሜቶች አማካይነት አይደለም ማለት ነው፡፡ መጀመሪያ በአካባቢው እንደሚያያቸው ሁሉም ነገሮች እቃዎችና ፍጥረቶች ነው የሚያየው፡፡ የሰውነት ትርጉም፣ ክብር፣ ወገንተኛነትና ወዘተ የተለያዩ እሴቶች ለእዚህ በቅድሚያ በአካልነት ላየነው ሰው የምናላብሰው መጀመሪያ እንደማንኛውም ነገር አጠገባችን ያለ ነገር መሆኑን ከተገነዘብን በኋለ ነው፡፡

ሌላውም ሰው እኛን የሚመለከተው እንደዛው ነው፡፡ ብዙ ጊዜ አንድ ሰው አትኩሮ ሲመለከተን እንረበሻለን፡፡ የሚረብሸን ሌላ ነገር አይደለም፡፡ ተመልካቹ እንደ ሰብአዊ ፍጥረት ሳይሆን እንደእቃ እየመረመረኝ ነው ከሚል ስጋት ነው፡፡  ሁሉን ነገር በቅድሚያ በግኡዝነት እንድናይ የሚደርገን አፈጣጠራችን በሰዎች መሃከል መኖር የሚገባውን ግንኙነት በሁለት ሰብአዊ ፍጥረቶች መሃከል በእኩልነት ሊኖር የሚገባው ግንኙነት እንዳይሆን አጥብቆ ይከላከላል፡፡ አንዱ ሌላውን እንዳልባሌ እቃ እንዳሻው ለማድረግ የመሻት ዝንባሌ ስለሚኖረው በሰዎች መሃከል ሚዛኑን የጠበቀ ሰብአዊ ግንኙነት ለመፍጠር ትልቅ ፈተና ነው፡፡

ይህ ተፈጥሯችን በአጠገባችን የምናየው ሰው፣ ከሌሎች ፍጥረቶች ሁሉ የተለየ እንደኛው በሰብአዊ ባህርያት የተሞላ ፍጥረት መሆኑን በምናውቅበት ወቅትም የማይለቀን ነው፡፡ ስለዚህም ከሰውነታችን ጋር የተጎናጸፍነውን ነጻነት ሊያጠፉ የሚፈልገው በውስጣችን ያለ ወደ ግኡዝነት/እቃነት የመቀየር ዝንባሌ ብቻ ሳይሆን ከውጭም አንዳችን ሌላውን በእቃነት የማየትም ዝንባሌ ይዘን የምንመጣ ፍጥረቶችም በመሆናችን ጭምር መሆኑን መረዳት ይገባል፡፡

እንግዲህ ከዚህ በላይ እንዳየነው ከውስጣችንም ይሁን ከውጭ በስብአዊ ነጻነታችን ላይ የሚካሄደው ወረራ ቀላል አይደለም፡፡ ይህንን ወረራ ለመመከት በሚገባ ካልተዘጋጀን፣  በራሳችን ምርጫ ይሁን ወይም በሌሎች ውሳኔ ከነጻነት ወደ ባርነት የምናደርገውን ሽግግር የሚስቆመው አይኖርም፡፡ የሰው ልጅ ለነጻነቱ ሁሌም ዘብ ይቁም የሚለው አባባል ለሰውነቱ ዘብ ይቁም ከሚለው አባባል ልዩነት የሌለው መሆኑን ልንረዳ ይገባናል፡፡

ሌሎች የነጻነት ፈርጆች፣ ማህበራዊና ዜጋዊ መብቶች ከዚህ ሰብአዊ ነጻነት የሚቀዱ ናቸው፡፡ ለእነዚህ መብቶቻችን መከበር የምናደርገው ትግል ለሰውነታችን ከምንሰጠው ክብር ጋር የተሳሰረ መሆኑን በሚገባ ስንረዳና ስናወቅ በቀላሉ ባርያ/እቃ አድርገው እንዳሻቸው ሊያደርጉን ለሚፈልጉ ሌሎች ሰዎች እጅ አንሰጥም፡፡ እኛም ብንሆን ሌላውን ሰው፣ በተመሳሳይ ሰብአዊ ክብሩን ገፈን እቃ/ባርያ አድርገን እንድናይ በውስጣችን የሚፈልቀውን ግፊት  በቀላሉ ስድ አንለቀውም፡፡

### የነጻነት ከህደትና የሸንገላ ህይወት

ነጻነታችን እራሱ አስፈሪ ሆኖ ስናገኘው ለገዛ ነጻነታችን ሃላፊነት ወስደን ከመፋጠጥ ነጻነት እንደሌለን አድርግን ማስመሰል እንደምንመርጥ አትተናል፡፡ እንዲህ አይነቱ አመለካከት እጅግ በርካታ ለሆንነው ሰዎች በውሸት ወይም በሸንገላ የተሞላ ህይወት እንድንኖር ያደርገናል፡፡ ነጻነትን ያክል ሰው የሚያደርገንን ታላቅ ጸጋ አስገፍፈንና ተገፈን ምንም ምንም እንዳልሆንን አስመስለን ለማለፍ እንሞክራለን፡፡ ችግሩ ግን የነጻነት ጉዳይ የምርምርና የጥናት ውጤት ሳይሆን ሰው ሆኖ ከመፈጠር ጋር የተያያዘ እርግማን በመሆኑ ሁላችንም እራሳችንን እያጭበረበርን እንደሆነ እናውቀዋለን፡፡

የነጻነትን ጉዳይ ፍርፋሪ እየለቀመ በውርደት የሚኖረው የኔ ቢጤ ያውቀዋል፡፡ የወያኔን ጌቶቹን አይንና ጆሮ ፈርቶ የሚኖረውም የዩኒቨርስቲ አስተማሪ ያውቀዋል። «እኔ አንድ ደሃ የእግዜር ለማኝ ነኝ ምን ማድረግ እችላለሁ?" የሚለው ደሃ በውስጡ የሚንቀለቀለውን በነጻነትና በእኩልነት ስብእናው ተከብሮ እንዲኖር ያለውን ማምለጫ የሌለውን ሰብአዊ ፍላጎቱን ቢፈልግ እንኳን ማጥፋት አይችልም። ከእዚህ ፍላጎት መሸሽ ካልሆነ ማምለጥ አይቻልም፡፡ በተመሳሳይም «እኔ የፖለቲካ ሰው አይደለሁም፡፡

(ክፍል 3 ሳምንት ይቀጥላል)

## የወያኔ ተለጣፊ ፓርቲ መሪዎች ኩብለላ ቀጥሉአል፣ ቶሎሳ ተስፋዬ አገር ጥሎ መጥፋቱ ተዘገበ

ወያኔ በምርጫ 97 ለሽንፈት የዳረጉትን ፖለቲካ ፓርቲዎች ለማፍረስ እንደመሳሪያ ከተጠቀመባቸው ሆድ አደሮች መካከል አንዱ የነበረው ቶሎሳ ተስፋየ፤ በዕውቀት ማነስ ምክንያት የተሰጠውን የአፍራሽነት ተልዕኮ በሚገባ ሊወጣ ባለመቻሉ ለመደለያ ተብሎ ተመቻችቶለት በነበረው የሙስና ቅሌት በመከሰሱ አገር ጥሎ ሊኮበልል እንደ ተገደደ ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ በላከልን ዜና ለማወቅ ተችሎል። የመቶአለቅነት ማዕረግ የነበረው ቶለሳ ተስፋዬ በዶክተር መረራ ጉዲና ይመራ የነበረውን የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ(ኦብኮ) ለማፍረስ ተሰጥቶት በነበረው ተልዕኮ በወያኔ ምርጫ ቦርድ እየታገዘ የኦብኮን ዋና መሥሪያቤት እና ህጋዊ የምዝገባ ፈቃድ ቀምቶ ሲንቀሳቀስ እንደነበረ የሚታወቅ ሲሆን በኦብኮ አባልነታቸው ምርጫ 97 ላይ ተመርጠው በወያኔ ፓርላማ ገብተው የነበሩትን ሳይቀር ለርሱ ተለጣፊ ድርጅት እውቅና ካልሰጡ በቀር በዕጩነት አቅርቦ ላስመረጣቸው ኦብኮና ለመረጣቸው ህዝብ ውክልና አንዳይኖራቸው ለማስደረግ የቻለ ክህደተኛ ሰው እንደነበር ይታወቃል።

ወያኔ የህዝብ ድምጽ በማጭበርበር የእራሱን ሥልጣን ለማደላደል ከተጠቀመባቸው አንዱ የሆነው ቶሎሳ ተስፋዬ የቅንጅትን ውህደት ለማደናቀፍ መሳሪያ እንደነበረው ልዴቱ አያለው ቀደም ሲል ኦብኮ ይገለገልባቸው የነበረባቸውን ማህተሞችንና ሰነዶችን በመውሰድ የራሱን ተለጣፊ ድርጅት ለማቋቋም የፖሊሶች ከለላ ተሰጥቶትና ሽጉጥ ታጥቆ የኦብኮ ጽህፈት ቤት ሠራተኞችን ጭምር አግቶ እንደነበር ይታወቃል።

መቶ አለቃ ቶለሳ ተስፋዬ ኦብኮን በማፍረስ ረግድ ለወያኔ በዋለው ውለታ ምክንያት ዜጎችን በአደባባይ በሽጉጥ ሲያስፈራራና ግልጽ በሆነ የመንግሥት ሃብት ዘረፋ ውስጥ ሲዘፈቅ ዝም ተብሎ እንደነበረ በመጨረሻ ግን ለወያኔ የሚሰጠው አገልግሎት አለመኖሩ ሲረጋገጥ ለክስ እንደተፈለገ በዚህም ምክንያት እግሬ አውጪኝ ብሎ ከአገር እንደወጣ ውስጠ አዋቂዎች ይናገራሉ።

በተያያዘ ዜና ወያኔ ቅንጅትን ለማፍረስ ከተጠቀመባቸው አንዱ የሆነው አየለ ጫሚሶ፤ በቅርቡ አገር ጥሎ መኮብለሉ ተዘግቦ እንደነበር ይታወሳል።

## ከ4 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ህዝቦቿ በአስቸኳይ የአለም አቀፍ ምግብ እርዳታ ስር የምትገኝ አገራችንን የሚመሩ የወያኔ ባለሥልጣናት "በአገራችን ረሃብ የለም" ማለት እንደጀመሩ ተዘገበ

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በሚከተለው የተሳሳተ የኢኮኖሞ ፖሊሲ ምክንያት ረሃብ አገራችንን ላለፉት 20 አመታት በተከታታይ ማጥቃቱ በድፍን አለም እየታወቀና፤ በየአመቱ ቁጥራቸው ከ4 ነጥብ 5 እስከ 15 ሚሊዮን የሚደርሱ ህዝቦቿ በአለም አቀፍ የምግብ እርዳታ የዕለት ህይወታቸውን እያቆዩ ባሉበት አገር የወያኔ መሪዎች አንድም ረሃብተኛ የለም ሲሉ መናገር መጀመራቸውን የወያኔ ዜና ማሰራጫዎች ዘግበዋል።

የአገዛዙ ቁንጮ መለስ ዜናዊ ከሁለት ሳምንት በፊት በአገሪቱ ውስጥ በረሃብ የሚሞት ሰው የለም ብሎ በአደባባይ ከተናገረ ወዲህ እያንዳንዱ የወያኔ ባለሥልጣን እንደገደል ማሚቶ እያስተጋባ ያለው ይህ አይናችሁን ጨፍኑና ላሞኛችሁ አይነት የጅል ቅጥፈት፤ ዕድገትና ልማት በአገሪቱ ውስጥ አስፍነናል የሚለው የወያኔ ፕሮፖጋንዳ በየአመቱ በረሃብ እንደቅጠል የሚረግፈውን ህዝብ ቁጥር ሊደብቅ ባለመቻሉ ለማደናገሪያ የተፈጠረ ሌላ ዘመቻ መሆኑ ታውቆአል።

ሰሞኑን ኢትዮጵያን ጎብኝተው የተመለሱ የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ ማህበራት ባለስልጣናት አስቸኳ መፍትሄ ካልተገኘ በስተቀር በርሃብ የተነሳ በኢትዮጵያ ብዙዎች ሊያልቁ ይችላሉ በማለት ስጋታቸውን በሚገልጹበት ባሁኑ ሰዓት፤ ዘረኛው መለስ ዜናዊ ራሱ በፈጠረው የረሃብ አደጋ የፖለቲካ ምስሉ እንዳይበላሽበት ከሹመት በሚገኝ የስልጣን ትርፍራፊ በዙሪያው ያሰባሰባቸውን ሆድ አደሮች በውሸት ዘመቻው ተሳታፊ አድርጎአቸዋል። ባለፈው ሃሙስ (ነሀሴ 12 2003 ዓ/ም) ምሽት ለአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ የአማርኛው ዝግጅት ክፍል በአገራችን ድርቅ እንጂ ረሃብ የለም በማለት በግብርና ምንስቴር የአደጋ መከላከል ዝግጁነትና የምግብ ዋስትና ዘርፍ ምንስትር ዴታ ተብዬው ምትኩ ካሳ ያደረገዉ ንግግር ባለፉት 20 የወያኔ አገዛዝ አመታት በደረሰው የረሃብ አደጋ ህይወታቸው የተቀጠፉ ዜጎችን ብቻ ሳይሆን ህይወታቸውን ለማቆየት ሲሉ ከአለም አቀፍ የምግብ እርዳታ መስጫ ጣቢያዎች የእለት ጉርሳቸውን ለመቀበል እየጎረፉ ያሉትን ዜጎች ኢትዮጵያዊነት የሚክድ ነው።

በ1966 በአገራችን ደርሶ በነበረው ተመሳሳይ የረሃብ አደጋ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች እንደቅጠል ሲረግፉ ንጉሱና በዙሪያቸው የተሰበሰቡት መኳንንቶች ልክ እንደዛሬው የወያኔ ባለሥልጣናት በአገራችን ምንም አይነት ረሃብ የለም በማለት ይክዱ እንደነበረ ታሪክ መዝግቦታል።

ይህ በዚህ እንዳለ በደቡብ ኢትዮጵያ ያለዉ የረሀብ አደጋ እጅግ አሳሳቢ እየሆነ መምጣቱ ተገለጸ:: በደቡብ ሶማሊያ ለተከሰተዉ የረሃብ አደጋ ከፍተኛ ትኩረት ስለተሰጠዉ በደቡብ ኢትዮጵያ የሚታየዉ የምግብ እጥረት እጅግ የከፋ መሆኑን በዉል እንዳይታወቅ አድርጎታል ሲል አሶስየትድ ፕሬስ የዜና አገልግሎት ገለፀ።

በምግብ እጥረት የተጎዱ ህፃናት በየእለቱ ወደ እርዳታ መስጫ ጣቢያዎች በመጉረፍ ላይ እንደሚገኙም ታውቆአል።ሸበዲኖ በተባለዉ የምግብ ማከፋፈያ ጣቢያ የሚገኙ የህክምና ባለሙያዎች እንደገለፁት ከአመት በፊት በምግብ እጥረት የተጎዳ ሰዉነት በአማካይ የነበራቸዉ ህፃናት ቁጥር አነስተኛ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ግን ቁጥሩ ከ9 እጥፍ በላይ ጨምሮአል ተብሎአል። ደቡብ ክልል በቁጥር ብዙ የሆኑ የብሄረሰብ አባላት ያሉበት ክልል ሲሆን በእያንዳንዱ ቤተሰብም ከስድስት ሰዉ በላይ ከመገኘታቸዉ ሌላ በመንግሰት የተያዙ አነስተኛ የእርሻ መሬቶችን በማረስ የሚተዳደሩ መሆናቸዉ ተገልጿል።

እንደዜና ምንጩ ዘገባ የመጪዉ የዝናብ ወቅት ሁኔታ በትክክል ስለማይታወቅ በመጪው አመት ባካባቢዉ ምን ያህል ሰዉ ለምግብ ርዳታ ይጋለጣል የሚለዉን መገመት አልተቻለም። ሆኖም በአገራችን ምንም ረሃብ የለም በማለት በረሃብተኛው ችግር መቀለድ የጀመረው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በአሁኑ ጊዜ አስቸኳይ እርዳታ የሚያስፈልጋቸዉ ሰዎች ቁጥር 250 ሺህ ብቻ እንደሆነ ይገልፃል።

በሌላ በኩል የአካባቢዉ የግብርና ቢሮ የስራ ሃላፊዎች ለ385 ሺህ ተረጂዎች የርዳታ እህል እንዲላክ ሲጠይቁ የአለም የምግብ ፕሮግራም 700 ሺህ ሰዎች የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ ርዳታ እንደሚያስፈልጋቸዉ ይናገራል።

## የአፍሪቃ የመሬት ቅርምት የዉሃ እጥረት ሊያስከትል ስለሚችል ገደብ ሊደረግበት እንደሚገባ ማሳሰቢያ ተሰጠ

በአፍሪካ የሚደረገዉ የመሬት ቅርምት በተለይም በምግብ እጥረትና በረሃብ በሚጎዱት የአፍሪካ አገሮች ላይ ችግር ሊያስከትል ስለሚችል አገሮች ለዉጭ ከበርቴዎች የሚሰጡት መሬት አስፈላጊዉ ገደብ ሊደረግበት እንደሚገባ በአንድ የባለሙያ አስተያየት ተገለፀ።

በአባይ ዉሃ ላይ ሙሉ በሙሉ ጥገኛ በሆነችዉ በግብፅ ህልዉና ላይ ሊያስከትል የሚችለዉ አደጋ ከፍተኛ በመሆኑ እንደ ኢትዮጵያና ሱዳን የመሳሰሉት አገሮች በረዢም አመታት ዉል ለዉጭ ድርጅቶች የሚሰጧቸዉ መሬቶች ለአካባቢዉ ሰላምና መረጋጋት አደጋ ሊኖረዉ እንደሚችል በተጨማሪ ተጠቁሟል።

በዚህም ምክንያት በ1960ዎቹ በህንድና በፓኪስታን መካከል በተፈረመዉ የኢንደስ የዉሃ ስምምነት ላይ የአለም ባንክ እንደረዳዉ ሁሉ፤ በመሬት ቅርምቱ ስምምነት ላይም አለም አቀፍ ጣልቃ ገብነት መኖሩ አስፈላጊ ነው ተብሎአል።

የምግብ ዋጋ ጭማሪ ፡ ድርቅና ረሃብ እጅግ አሳሳቢ በሆነ ደረጃ በደረሱበት ወቅት አበባ እና ሌሎች ለነዳጅ ዉጤት የሚዉሉ እፅዋትና ሰብሎችን ለማብቀል ለዉጭ ከበርቴዎች በሚሰጡ መሬቶች ላይ የሚደርሰዉ የከርሰ ምድር ዉሃ እጥረት ለአገሮቹ ለራሳቸዉ ከፍተኛ ችግር ሊሆን እንደሚችል በተለያየ ጊዜ በባለሙያዎች በመገለጽ ላይ እንዳለ ይታወቃል።

## ኤርትራ አልሸባብን እንደማትረዳ አምኛለሁ ሲሉ የዩጋንዳው መሪ አስታወቁ

ዩዩጋንዳው መሪ ዩዎሪ ሙሴቬኒ የኤርትራውን መሪ ኢሳያስ አፈወርቂን ጉብኝት ከአስተናገዱ በሁዋላ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ኤርትራ አልሸባብን እንደማትረዳ ፕሬዚዳንት ኢሳያስ ነግረውኛል፤ እኔም አምኛቸዋለሁ፤ ፕሬዚዳንት ኢሳያስ ተራ ሰው ሳይሆኑ ሊከበሩ የሚገባ ጓድ ናቸው ብለዋል።

የፕሬዚዳንት ሙሴቬኒ ንግግር በኤርትራ ላይ ማእቀባ ለማስጣል ደፋ ቀና የሚለውን የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ወሽመጥ የሚበጥስ እንደሆነና እንደ ከአሁን ቀደሙ ኤርትራን ለማጥቃት ኢጋድን እንደመሳሪያ መጠቀም እደጋ እየገጠመው መምጣቱን ያሳያል የሚሉ አስተያየቶች እየተሰነዘሩ ነው።

የፕሬዝዳንት ሙሰቪኒን መግለጫ ተከትሎ አስከዛሬ ከወያኔ የተሰጠ ምንም አይነት ይፋዊ ቃል ባይኖርም በኢጋድ ድጋፍ የሚተማመነው መለስ ዜናዊን እጅግ ሊያስከፋ እንደሚችል ውስጥ አዋቂዎች ይናገራሉ። አይጋ ፎረም በመባል የሚታወቀው የወያኔ ፕርፖጋንዳ ድህረ ገጽ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በጅግነታቸው ሲያሞካሻቸው የነበሩትን ፕሬዚዳንት ሙሴቬኒን አምባገነን ናቸው ሲል የስድብ ናዳውን እንዳወረደባቸው ይህም ወያኔዎች ስለ ፕረዝደንት አፈወርቂ ጉብኝትና በዩጋንዳ ስለተደረገላቸው ወዳጃዊ አቀባበል አለመደሰታቸውን ያመለክታል ተብሎአል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz
እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:00 እስከ 2:30 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን። **ማሳሰቢያ**:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org